ሴፕቴምበር 6፣ 2016

ውድ የደቡብ /South/ ሁ/ደ/ት/ቤትወላጆች፦

ከተማሪዎች ጋር የተገናኙ የደህንነት እና የፀጥታ ክስተቶችን ለእናንተ ማሳወቅ ተቀዳሚ ተግባራችን ነው። እናም ይህን ደብዳቤ መጻፋችን እሁድ ሴፕቴምበር 4 ከጧቱ 9:30 (ኤ.ኤም) ሰዓት ሁለት ሰዎች ከደቡብ /South/ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዕቃዎችን ለመስረቅ ሲሞክሩ በፖሊሶች መያዛቸውን ለመግለጽ ነው። ግለሰቦቹ በት/ቤቱ በአንደኛው መስኮት ሰብረው ገብተው በዋናው ቢሮ (ጽ/ቤት) ውስጥ ፖሊስ ሊይዛቸው ችሏል። እነዚህ ሁለት ሰዎች በዋና የዘረፋ ወንጀል ይከሰሳሉ።

ይህ ክስተት በመድረሱ በእውነት አዝነናል፤ እናንተንም ሊያስጨንቃችሁ እንደሚችል እንረዳለን። እናም ሁለቱም ሰዎች የተያዙ እና የሚከሰሱ መሆናቸውን በድጋሜ እንገልጻለን።

ማንኛውም ጥያቄ ወይም ሀሳብ ካላችሁ እንደተለመደው እኛን ለመጠየቅ ምንም ወደኋላ እንዳትሉ።

ከሰላምታ ጋር!

ጄኒፈር ሃንሰን /Jennifer Hanson/
ርዕሰ መምህር